# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

ሚያዚያ ፳፰ ፪ሺ፩ ዓ.ም
May 7 2009

## ትኩረታችን በሕዝብና በሀገር ዋና ጠላቶች ላይ ይሁን

የሕብረተሰብ የዕድገት ጉዞ ያሉት ቅራኔዎች በይነግብር ውጤት ነው፡፡ ቅራኔዎች ዕድገትን ይወልዳሉ፤ ተፃራሪ ጥቅሞችን የሚያንፀባርቁ በሚያደርጉት ትግልና ፉክክር ዕድገት ሊመጣ ይችላል፡፡ ፈሳሽ ውሀ አይበሰብስም እንደሚባለው ነው፡፡ በአንፃሩ ቅራኔዎች በአግባብ ካልተያዙ ለወደፊት ጉዞና ዕድገት ምንጭ መሰረት መሆናቸው ይቀርና፤ ቀውሶች በሚገባ ተይዘው ለውጥን አዋላጅ እንዲሆኑ ካልተደረገ ውድቀትና ድቀት፤ ጥፋትና ፍጅት ሊከተል ይችላል፡፡ በሕዝብ መሀል ያለ ቅራኔ መለስተኛ በመሆኑ በጥንቃቄ ተይዞ በሰላምና፤ በዴሞክራሲ ሊፈታ የሚችልና የሚገባም ነው፡፡ ካልሆነ የርስ በርስ ግጭትን ይወልዳል፡፡ በሕዝብና በጨቋኝ ገዢዎች መሀል ያለው ቅራኔ ግን በሰላም የሚፈታ ወይም በዕርቅ የሚዳኝ ሳይሆን በጨቋኞች መወገድ ብቻ ሊጠፉ የሚችል ነው፡፡ ለዚህም ነው የቅራኔዎችን ጠባይና አያያዝ ማወቁ ወሳኝና ቀዳሚ ጉዳይ ሆኖ የሚገኘው፡፡ ለዚህም ነው በቅራኔዎች ላይ የተዛባ ግንዛቤና አቅዋም መያዙ ሕዝብን ለቀጣይ ባርነትና ጭቆና የሚዳርግ የሚሆነው፡፡

ከሕዝብና ከሕዝብ ትግል አንፃር ስንነሳ በሕዝብ መሀል የሚከሰቱ ቅራኔዎችን በመለስተኛ ደረጃ መያዛቸው በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የወያኔ ቡድን በሕዝብ መሀል ያለውን ቅራኔ ዋነኛ አድርጎ በመፈረጅ ብሄረሰቦች በሰላም አብረው ሊኖሩ አይችሉምና መገንጠል መለያየት አለባቸው ብሎ በርኩስ ድምዳሜው መሰረት ሕዝብን እነሆ እስከዛሬ ከፍሎ እያናከስ አለ፡፡ ለወያኔ አገዛዝ ዕድሜ መራዘም ምክንያቶቹ ከሆኑት ውስጥ (አፈናው፤ የባዕዳን ድጋፍ፥ ...ወዘተ) አንዱ የሕዝብ ጎራ መከፋፈሉ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ከዚህ ቀደም ተማሪዎች ለምሳሌ በጋራ ሆነው ሥርዓቱን በመታገል ለሕዝብ መብት መከበርና ለሀገር ልዕልና ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረጉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን ተማሪዎችን የወያኔ አገዛዝ በብሄረሰብና በሃይማኖት ከፋፍሎ በጋራ እንዳይነሱበት ማድረጉ የሚካድ አይደለም፡፡ ወያኔ ለሥልጣን ሲበቃም የፖለቲካ ኃይሎችን በብሄረሰብ ደረጃ እንዲፈሉ በማድረግ በኢትዮጵያዊነት ለኢትዮጵያ መታገልን ሸርሽሮና አዳክሞ፤ የየክልል ዘመናዊ መኳንንትን ፈልፍሎ ክፍፍልን ማንገሱም የታየ ነው፡፡ በጋራ የወያኔን አገዛዝ መታገል ሲገባ የሚመለከተኝ የብሄረሰቤ ጉዳይ ብቻ ነው ማለት ፈሊጥ ሆኖ፤ ይባስ ብሎ ኢትዮጵያዊነትን ራሱን መካድ ማሳፈሩ ቀርቶ በዚህም በዚያም የሚስተገባ ሆኖ የተናጠል ትግልና የርስ በርስ መነካከሱ በዝቶ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ከዚህ ሌላ ራሳቸውን ሀገር ወዳድ ወይም

የአንድነት ሀይሎች የሚሉትም ቢሆኑ በመሰረቱ ዋናው ተግባርና ተልዕኮ ሀገርን ከጥፋት ማዳንና ዴሞክራሲን ማስፈን ሆኖ ሳለ መስማማት አቅቷቸው ትግላቸው መዳከሙ ሲታይ የቆየ ነው::

በድርጅቶች መሀል ቅራኔ መኖሩ የሚያስደነግጥ ሳይሆን የሚጠበቅ ነው:: ድርጅት የሰዎች ስብስብ ነው:: ድርጅት በተወሰነ አቅዋም ዙሪያ የሚሰባሰቡ ሰዎች መሳሪያ ነው:: በመሆኑም የህብረተሰቡ ቅራኔዎች በሰዎች ላይና በሰዎች የሚንፀባረቁ ናቸውና ልዩ ልዩ ፍላጎቶች÷ አቅዋሞችና ጠባዮች መጋጨታቸው ወይም መለያየታቸው አይቀርም:: ችግሩ ይህ ሀቅ መሆኑ ሳይሆን ቅራኔዎቹ ወደ ከረረ ግጭት ተሸጋግረው ጠላትነትን እንዳይፈጥሩ ማድረጉ ላይ ነው:: ድርጅቶች ልዩነታቸውን በአግባብ ይዘው ዋና ትኩረታቸውን በጋራ ወይም በዋናው የሀገርና የሕዝብ ጠላት ላይ ማድረግ አለባቸው ማለት ነው:: ይህን ማድረግ ባለመቻሉ ወይም በማይችሉበት የሕዝብ ትግል ይጎዳል፤ በእርስ በርስ ንትርክና ግጭት ይዳከማል:: በመሰረቱ ድርጅቶች ማን የጋራ ጠላት ነው፤ ማን የሕዝብ ጠላት ነው በሚለው ላይ የጋራ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል:: የወያኔ አገዛዝ የሕዝብ ወዳጅ ነው የሚሉና የለም ጠላት ነው የሚሉ ዕይታቸው ሊገጥምና ሊስማሙ አይችሉም:: እንዲስማሙም መጠበቅ የለበትም:: የሕዝብን ጠላት ወዳጅ የሚሉ ስህተታቸው በተራ ግምገማ ስህተት ደረጃ ብቻ የሚፈረጅ ሳይሆን የተለጣፊነትንም ተውሳክ የሚያሳይ ሊሆን መቻሉ ግልፅ ነው:: ስለዚህም ድርጅቶች የርስ በርስ ልዩነታቸውን በአግባብ መያዝ አለባቸው ስንል ፀረ ወያኔ አገዛዝ የሆኑትና ለኢትዮጵያ አንድነት የቆሙት ዴሞክራሲያዊ ኃይሎችን ማለታችን ነው:: ይህን ስንልም አጥብቀን የምንቃወመውን ድርጅታዊ ትምክህት በሌባ ዝንብ ደረጃም ቢሆን ልናየው የምንፈልገው ባይሆንም ድርጅት ስንል ድርጅታዊ ህልውናና ሚዛን ያላቸው ማለታችን መሆኑን ጫና መስጠት እንገደዳለን:: አንድ ራሳቸውን ድርጅት የሚሉ ወይም ሁለት ሶስት የወያኔ ተለጣፊዎች ድርጅት እየተባሉ ያለው ክስተት ተቀባይነትን መነፈግ ያለበት ነው::

ድርጅቶች ይተባበሩ ወይም ይሰባበሩ ሲል የተደመጠ "ሕዝብ" መኖሩ ዛሬም አነጋጋሪ ቢሆንም ሀገር ወዳድ ድርጅቶች በተናጠል ከሚታገሉ በህብረት ቢታገሉ ውጤቱ የተሻለ ለመሆኑ ክርክር አያስፈልገውም:: በዚህም መሰረት ልዩ ልዩ ህብረቶች ከ1965 ዓ.ም. ጀምሮ በየጊዜው ተሞክረው በየፊናቸው ጠቀመውም አልፈዋል:: ዘላቂነትን መጎናፀፍ ያልቻሉባቸውም ምክንያቶች ሀቅ ይሁኑ ሌላ በየጊዜው በየድርጀቶቹ የቀረቡ ናቸው:: ሊያብሩ የሚችሉ ድርጅቶች መተባበር ወይም በህብረት መሥራት ከቻሉ ሊበረታቱ ይገባቸዋል:: ህብረትም ቅንጅትም መሰረቱ ካላማረ ግን ውጤታማ ሳይሆን ቀርቶ ችግርና ክፍፍልን ቀፍቃፊ ሊሆን መቻሉ ደግሞ የቅርብ ጊዜ ተመክሮአችን ነው:: ስለዚህም ሁሉም ድርጅቶች በግድ ህብረት መመስረት አለባቸው ወይም በህብረት መግባት አለባቸው የሚል አጣብቂኝ ሁኔታ መኖር አይገባውም:: እበትና የበሰበሰው ሁሉ ለትል ያመቻል እንደተባለው የወያኔ አገዛዝ በድርጀቶች መሀል ችግር ባለበት ሁሉ የደራ ገበያን ያገኛል:: ቅጥረኞችንና ሰርጎ ገቦችን በማሰማራት ቀውሱንና ቅራኔውን ያባብሳል፤ ያናክሳል፤ ሊታረቅ የሚችለውንና የሚገባውን ቅራኔ ወደ ከባድ ውጥረትና ቀውስ ለውጦ

ድርጅቶች በጠላት ላይ ማተኮርን ትተው በእርስ በርሱ ግጭት ላይ እንዲረባረቡ ያደርጋል፡፡ ዛሬ በተለይ በባዕድ ሀገሮች የድርጅቶች ደጋፊ ነን በሚል ሽፋን በወያኔ ላይ ሳይሆን ነጋ ጠባ በሌሎች ፀረ ወያኔ ድርጅቶች ላይ የሚዘምቱ የዚሁ ምሳሌ ናቸው፡፡ አውቀው ተቀጥረውና ተከፍለው ባልሆነበት ደግሞ ተጃጅለው በወያኔ በእጅ አዙር ተቃኝተው በዚህ አሳፋሪና ጎጂ ተልዕኮ የተሰማሩ ናቸው፡፡ ይህ ድርጅት ከዚያኛው ለምን በጠላትነት ይተያያል ብለን በምር ምርምር ብናደርግ ምክንያቶችን የምናጣበት ምክንያት መለስተኛ ልዩነቶችን የማስተናገድ ችሎታና ትዕግሥት ጠፍቶ ለወያኔ በር ተከፍቶ የክፍፍል መርዙን እንዲረጭ ዕድል ስለተሰጠው ሆኖ እናገኛለን፡፡ ስለዚህም በመጀመሪያ ደረጃ ይህን ሁኔታ መለወጥና ሀገር ወዳድ ድርጅቶች እርስ በርስ መጠላለፉንና መነታረኩን ማቆም አለባቸው ማለት እንፈልጋለን፡፡ ድርጅታዊ ትምክህትም ገበናን አጋልጦ ከመ ጤዛ የሚተን መሆኑን በቅርቡም ያየነው ነውና ዛሬም ሊሰፍን ዕድል ባይሰጠው ይመረጣል፡፡ ፖለቲካ አቅዋሞችን በተሳሳቱበት ወይም ተሳስተዋል መስመር ስተዋል ጎጂ ሆነዋል ብሎ በተደመደመበት መተቸት ከመብት አልፎ ግዴታ መሆኑ መረሳት የሌለበት ቢሆንም ልዩነትን በአግባብ ይዞ ለመፈራቀቅና ለመጋጨት ሳይሆን ገንቢ በሆነ መንገድ ለመተራረም በተቃኘ መንፈስ መንቀሳቀሱ የሚመረጥ ነው፡፡

ኢሕአፓ የዳበረ የህብረት ትግል ተመክሮ ያለው ሲሆን በአብላጫው ለተገኘው ድል ሳይመሰገን ለደረሰው ችግር ግን ሲወቀስና ሲወገዝ መደመጡም የተለመደ ሆኗል፡፡ ቢሆንም ድርጅቱ በህብረት ግንባር መስክ ያለውን ተመክሮ በየፈርጁ ገምግሞ ያቀረበ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ኢሕአፓ ከፀረ ወያኔ አገዛዝ ድርጅቶች ጋር ሁሉ በሰመረና በተባበረ መንገድ ለመታገል ሁሌም ፍላጎቱን የገለጠ ሲሆን ካሳለፋቸው ተመክሮዎች በመነሳት ደግሞ ሕዝብን በስፋት የሚያስተባብር ፖለቲካየማስፈኑን እንቅስቃሴ አስቀድሞ ለመታገል ሲጥር ቆይቷል፡፡ ይህ በራሱ የሚያካሂደው ድርጅታዊ እንቅስቃሴ እንዲጠናከር በሀገር ውስጥ በህቡዕ በባዕድ ሀገርም በይፋ እየታገለ አለ ፡፡ በአሁኑ ጊዜ  የወያኔ አገዛዝ የአፈና ጥርሱን ስሎ ሕዝብንና ታጋይ ኃይሎችን ሊቦጫጭቅ እየተቅበዘበዘ ባለበት ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች ማለትም <u>የወያኔ አገዛዝ በሁለገብ ትግል ተወግዶ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን አለበት የሚሉ ኢትዮጵያዊ ኃይሎች ሁሉ</u> በመሀላቸው ክፍተት ሳይፈጥሩ፣ ልዩነቶችን በሁለተኛ ደረጃ ይዘውና በሥርዓት እየፈቱ፣ ቅራኔን የሚያባብሱ ወዳጅ መሳይ አፍራሾችንና የወያኔ ሰርጎ ገቦችን እያገለሉ በጋራም ሆነ በየራሳቸው ለሀገርና ለሕዝብ የሚደረገውን ትግል ማጠናከር አለባቸው፡፡ ለዚህ ዓላማ ኢሕአፓ ተባባሪ መሆኑን እየገለፀ ሁሉም ኃይል ዋና ትኩረቱን በዋናው የሀገርና የሕዝብ ጠላት ማለትም በወያኔ አገዛዝ ላይ እንዲያደርግ ጥሪ ያቀርባል፡፡

EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

E-mail ESPIC@aol.com

Website: http://www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France